የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

ሰመጉ

# 146ኛ ልዩ መግለጫ

## በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

ታህሳስ 24 ቀን 2011 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146

ሰመጉ


ዋናው ጽ/ቤት፡ አዲስ አበባ
አ.አ ስታዲየም ፊትለፊት፣ ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ ቢሮ ቁጥር 19
ስልክ: (+251) 011 558-2387
ፋክስ: (+251) 011 551-7704
ኢሜይል: info1hrco@gmail.com info@ehrco.org
ድረ ገጽ: www.ehrco.org
ፌስቡክ፡ https://www.facebook.com/humanrights.council.5?ref=bookmarks
ትዊተር : @hrcoethio
የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ
ስልክ: (+251) 011 558-2387
ኢሜይል: info1hrco@gmail.com /monitoring@ehrco.org


**ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች**

| | |
|---|---|
| ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ ፖ.ሳ.ቁ 360 |
| ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ ፖ.ሳ.ቁ 1115 |
| ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ነቀምቴ - ስ.ቁ (+251) 057 660-2664፣ ፖ.ሳ.ቁ 463 |
| ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | ድሬደዋ - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ ፖ.ሳ.ቁ 2596 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡ | አዲስ አበባ- ስ.ቁ (+251)011 551-7704፣ ፖ.ሳ.ቁ 2432 |
| መቀሌ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ፡ | መቀሌ- ስ.ቁ (+251) 0342413696 |

**ማውጫ**

1. ኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ ........ 4

2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ........ 5

3. መግቢያ ........ 5

4. የልዩ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች ........ 7

4.1. የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ ........ 7

4.2. ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ ........ 8

4.3. በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ ........ 8

4.4. የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች ........ 8

4.5. የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ........ 9

5. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጉጂ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጌዴኦ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በሲዳማ እና ወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆችና አባላት መካከል በተፈጠሩ ጥቃትና ግጭቶች ምክንያት የተፈፀሙ የተለያዩ የሙብት ጥሰቶች ........ 10

5.1 በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ) ........ 10

5.2 የአካል ጉዳት፡- በጥይት ማቁሰልና ድብደባ ........ 14

7. ማሳሰቢያ ........ 22

1. ኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ[1]




የመብት ጥሰቱ የተፈጸመባቸው አካባቢዎች

[1] ኢትዮጵያ [ካርታ]. <http://www.h2empower.org/aboutus/factsethiopia.html>. (August 11, 2015)

## 2. የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ)፣ የቀድሞው የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 621/2001 መሠረት ኢትዮጵያዊ የበጎ አድራጎት ማኅበር ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው። ሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው።

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት፣ ሰመጉ ላለፉት 27 ዓመታት ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፤ በማከናወንም ላይ ይገኛል። የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም መብት የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል። በተጨማሪም ሰመጉ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤ ውጤቶቹን በስብሰባዎችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ያሠራጫል፤ የአድቮኬሲ ሥራዎችንም ያከናውናል፤ በነዚህም በፖሊሲዎችና በአፈጻጸማቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳደር ይጥራል።

የሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል። ከሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ ማረሚያ ቤቶችንና የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሂደት በመከታተል ፍትሐዊነታቸውንና በአጠቃላይም የዳኝነት ነጻነት መኖሩን መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል። ከነዚህ በተጓዳኝ ሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

ሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና አቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ ተግቶ በመሥራት ላይ ይገኛል።

## 3. መግቢያ

በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጉጂ ዞን እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጌዴኦ ዞን ከሚገኙ አዋሳኝ አካባቢዎች የሚኖሩ ሕዝቦች አብሮ በመኖር፣ በጋብቻና በመፈቃቀር እንዲሁም የጌዴኦ ማህበረሰቦች በጉጂ ዞን ክልል ውስጥ ለበርካታ አመታት አብረው በሰላም ሲኖሩ ነበር። ምንም እንኳን አልፎ አልፎ በአካባው የሚነሱ ግጭቶች ቢኖሩም ባፉት ጊዜያት በሃይማኖት መሪዎችና በሃገር ሽማግሌዎች ችግሮቹ

ሲፈቱ ኖረዋል፡፡ ዳሩ ግን ባለፉት 27 ዓመታት በተለያየ ጊዜ ግጭቶችና ጥቃቶች በአካባቢው በመከሰታቸው ዘርፈ ብዙ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተከስተዋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ሕዳር 19 ቀን 1991 ዓ.ም ባወጣው 13ኛ መደበኛ መግለጫው በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ሃገረ ማርያም ወረዳ በሚገኙ የጉጂና የጌዴኦ ማህበረሰቦች ተሰባጥረው በሚኖሩባቸው በርካታ የቀበሌ ገበሬ ማህበራት በተከሰተ ግጭት ከሁለቱም ማህበረሰቦች የበርካታ ዜጎች ሕይወት መጥፋቱን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ ከፍተኛ ንብረት መውደሙን እንዲሁም ዜጎች ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውን ገልጿል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ‹‹በአዋሳና አካባቢው በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ የደረሰ አስከፊ የመብት ረገጣ›› በሚል ርዕስ ግንቦት 21 ቀን 1994 ዓ.ም ባወጣው 51ኛ ልዩ መግለጫው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ የሲዳማ ዞን መስተዳድር ከአዋሳ ከተማ ወደ አለታ ወንዶ እንዲዘዋወር ተወስኗል በሚል የሲዳማ ብሔረሰብ ተወላጆች ቅሬታቸውን ለመንግስት በሰላማዊ ሰልፍ ለመግለጽ በመሞከራቸው በታጠቁ የመንግስት ኃይሎች በተወሰደ እርምጃ በርካታ ሰዎች ሕይወታቸውን እንዳጡ ገልጿል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ነሐሴ 1998 ዓ.ም ባወጣው 25ኛ መደበኛ መግለጫው በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን አዶላ፣ ኦዶ ሻኪሶና ቦሬ ወረዳዎች ከተለያዩ የሃገሪቷ አካባቢዎች መጥተው በተለያዩ የስራ መስክ ተሰማርተውና ንብረት አፍርተው በሚኖሩ ዜጎች ላይ ከየካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የሌላ ብሔረሰብ ተወላጆች ይውጡ የሚል ቅስቀሳ በመካሄዱ የሌላ ብሔረሰብ ተወላጆች ለተለያዩ የንብረት ውድመትና ከቤት ንብረት መፈናቀል መዳረጋቸውን ገልጿል፡፡ በተያያዘም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጌዴኦ ዞን በሚገኙ በይርጋጨፌ፣ ፍስሃገነት፣ ጨለለቅቱ፣ ቡሌ እና ዲላ ከተሞች በሚኖሩ የሌላ ብሔረሰብ ተወላጆችን ለጥቃት በሚያጋልጥ መልኩ ከመጋቢት 28 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ለስምንት ቀናት ያክል በቡድን በተደራጁ አካላት ‹‹መጤ ይውጣ›› የሚል ቅስቀሳ በመጀመሩ የዜጎች ሕይወት መጥፋቱን፣ የአካል ጉዳት መድረሱን፣ ከፍተኛ ንብረት መውደሙን እንዲሁም ዜጎች ከቤት ንብረታቸው መፈናቀላቸውን ገልጿል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ሚያዚያ 22 ቀን 1999 ዓ.ም ባወጣው 100ኛ ልዩ መግለጫው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጌዴኦ ዞን በሚገኙ በይርጋጨፌ፣ ፍስሃገነት፣ ጨለለቅቱ፣ ቡሌ እና ዲላ ከተሞች በሚኖሩ የሌላ ብሔረሰብ ተወላጆች ላይ በተፈጸመው ጥቃት የተነሳ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የመልሶ ማቋቋም ስራ በተገቢው ሁኔታ እንዲሰራና የሰብዓዊ መብት ጥሰት የፈጸሙት ግለሰቦችና አካላት ለፍርድ እንዲቀርቡ በድጋሚ አሳስቧል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ባወጣው 27ኛ መደበኛ መግለጫው በኦሮሚያ ክልል ከደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጋር በሚያዋስኑት የጉጂ ዞን ቡሌ ሆራ ወረዳና በአዋሳኙ ቡርጂ ልዩ ወረዳ የሚኖሩ የጉጂና ቡርጂ ማህበረሰብ አባላት የመሬት ይዞታ ይገባኛል ጥያቄ ተገቢውን መፍትሄ ባለማግኘቱ የካቲት 20 ቀን 1999 ዓ.ም በተነሳ ግጭት ከሁለቱም ማህበረሰቦች በርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት መድረሱን ግልጿል፡፡ እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጌዴኦ ዞን ዲላ ኡሪያ ቱምቲቻ ቀበሌ ታህሳስ 04 ቀን 1999 ዓ.ም በተነሳ ብሔርን መሰረት ባደረገ ግጭት በርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት መድረሱን ገልጿል፡፡

በቅርብም የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ‹‹በኢትዮጵያ ለብሔረሰብ ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች የማያዳግም የፖሊሲና የአፈጻጸም መፍትሔ ይሰጥ›› በሚል ርዕስ ጥቅምት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ባወጣው 143ኛ ልዩ መግለጫ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ጌዴኦ ዞን በሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች የተፈጸመውን ብሔርን መሰረት ያደረገ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት በአስቸኳይ እንዲቆሙና የማያዳግም መፍትሄ እንዲሰጣቸው አሳስቧል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ጳጉሜ 04 ቀን 2009 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ‹‹ከማንነት፣ ከአስተዳደርና ከድንበር ይገባኛል ጥያቄ ጋር በተያያዘ በኦሮሚያ ክልል የጉጂ ኦሮሞ ገላና፣ አባያና ቡሌ ሆራ ወረዳዎች አዋሳኝ አካባቢዎችና በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ አዋሳኝ አካባቢዎች ላይ ግጭት ተፈጥሮ በርካታ ሰብዓዊና ቁሳዊ ጉዳት መድረሱን ገልጾ በድጋሚ ሰኔ 22 ቀን 2010 ዓ.ም ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ ክልል የሲዳማ ማህበረሰብ የሚያከብረውን የፍቼ ጫምባላላ በዓል ምክንያት በማድረግ በሲዳማና በወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆች መካከል በተፈጸመ ጥቃትና ግጭት እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ብሔረሰብ እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጌዴኦ ብሔረሰብ አባላት መካከል በተፈጠረ ጥቃትና ግጭት የበርካታ ሰዎች ሕይወት መጥፋቱን፣ አካል መጉደሉን፣ ንብረት መውደሙን እና ዜጎች ከመኖሪያ ቀዬአቸው መፈናቀላቸውን አካትቷል፡፡

ለብሔር ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ፣ ይህንኑ ለመከላከልም አስፈላጊው የህግና ተቋማዊ ስራ ባለመሠራቱ ቀውሱ ተባብሶ አሁንም ድረስ አስከፊና አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ይህንንም ተከትሎ እየተፈጸመ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ለመረዳት የሚያስችሉ በርካታ ማሳያ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) በተደጋጋሚ በሚያነሳቸው የተለያዩ አይነት መግለጫዎቹ መንግስት ግጭቶች ከመከሰታቸው በፊት አስፈላጊ የሆነ የጥንቃቄ እርምጃዎችን እንዲወስድ በተደጋጋሚ በአንድ አካባቢ እየተቀሰቀሱ የሰው ህይወት፣ የአካል ጉዳት እና የንብረት ውድመት የሚያስከትሉ ግጭቶችን መነሻ ምክንያታቸውን ህብረተሰቡንና ምሁራንን በማሳተፍ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ሲጠይቅና ሲያሳስብ ቆይቷል፡፡ እነዚህ ተደጋጋሚ ጥሪና ማሳሰቢያዎች ችላ በመባላቸው የበርካቶች ህይወትና ንብረት ጠፍቷል፣ አካል ጎድሏል፣ ንብረት ወድሟል እዲሁም ዜጎች ቤት ንብረታቸውን ጥለው ለመሰደድ ተገድደዋል፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በሐገራችን በርካታ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች በርካታ የብሔር ጥቃቶችና ግጭቶች እየተካሄዱ፣ ብሔር ተኮር የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ በመምጣታቸው ሁኔታው ተባብሶ መዳረሻውን ለመተንበይ የሚያስቸግር አስከፊ ብሔራዊ ቀውስ ከመፈጠሩ በፊት መንግስት ዘላቂና የማያዳግም መፍትሄ ይስጥ በማለት ሰመጉ በዚህ 146ኛ ልዩ መግለጫ ጥሪውን በድጋሚ ያስተላልፋል፡፡

## 4. የልዩ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች

### 4.1. የልዩ መግለጫው ዋና ዓላማ

የዚህ ልዩ መግለጫ አቢይ አላማ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጉጂ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጌዴኦ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በሲዳማና ወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆችና አባላት መካከል በተፈጠሩ ጥቃትና ግጭቶች ምክንያት እየተፈጸሙ ያሉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ መፍትሄ እንዲሰጣቸው፣ ጥሰቶች እንዲቆሙና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የመከላከል እርምጃ እንዲወስድ ለማሳሰብ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሳ እንዲሰጣቸውና ድርጊቱን የፈጸሙና ያስፈጸሙ አካላት በህግ እንዲጠየቁ፣ ጥሰት ፈጽሞ ሳይጠየቁ መቅረት እንዲቆምና ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች በድጋሚ የማይፈጸሙበት የፖሊሲና የአሰራር ማስተካከያዎችና እርማቶች ከወዲሁ እንዲደረጉ መጠየቅና መጎትጎት ነው፡፡

በተጨማሪም ይህ መግለጫ በማናቸውም መልኩ ለማንኛውም አይነት ጥቃትና ግጭት መቀስቀሻነት፣ ጥላቻን ለመፍጠር እና ሠላምን ለማደፍረስ መዋል እንደሌለበት ሰመጉ ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሳስባል፡፡ በመሆኑም ይህ ልዩ መግለጫ ከላይ ከተዘረዘሩት አላማዎች ውጪ ህጋዊ ላልሆኑ እንዲሁም በጐ ህሊናን እና መልካም ባህልን ለሚቃረኑ ተግባራት በሌሎች ወገኖች አማካኝነት ተግባር ላይ ቢውል የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡

### 4.2. ምርመራውና ልዩ መግለጫው የተመሠረተበት የህግ ማዕቀፍ

በዚህ ልዩ መግለጫ ውስጥ ይፋ የተደረጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዓይነትና ዘርፍ ለመረዳትና ለማሳየት በዋና መሠረትነት የሚያገለግሉት፣ የኢፌዴሪ ህገ መንግስት፣ የአፍሪካ የሰዎችና የህዝቦች መብቶች ቻርተር እና ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ግዴታም የገባችባቸው የተለያዩ የዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ናቸው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በየዘርፋቸው በተገለጹበት ቦታ ሁሉ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በመነሻነትና በማመሳከሪያነት ተጠቅሰዋል፡፡

### 4.3. በምርመራው የተሸፈኑ አካባቢዎችና ምርመራው የተካሄደበት ጊዜ

ይህ 146ኛ ልዩ መግለጫ የሚመለከተው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጉጂ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጌዴኦ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በሲዳማና ወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆችና አባላት መካከል በተፈጠሩ ጥቃትና ግጭቶች ምክንያት የተፈጸሙትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነው፡፡ የመብት ጥሰቶች የተፈጸሙት ከሚያዝያ ወር 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 2010 ዓ.ም ድረስ ሲሆን ሰመጉ ባለሙያዎቹን ወደ አካባቢው ልኮ የማጣራት ሥራውን የሰራው ከሐምሌ 01 እስከ ሐምሌ 15 ቀን 2010 ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ነው፡፡ ሰመጉ ለዚህ መግለጫ የበቁ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ምርመራ ያካሄደባቸው ወረዳዎች ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ በዝርዝር ተመልክተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ዞኖችና ወረዳዎች

| ተ.ቁ | የክልሉ ስም | ዞን | ወረዳ/ ከተማ |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ ክልል | ምእራብ ጉጂ ዞን | ቀርጫ |
| | | | ቡሌ ሆራ |
| 2 | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል | ሲዳማ ዞን | ሀዋሳ |
| | | | ቱላ |
| | | | ለኩ |
| | | | ይርጋለም |
| | | | ወንዶገነት |
| 3 | ደ/ብ/ህ/ክልል | ወላይታ ዞን | ሶዶ |
| | | | ሉካ አባያ |
| 4 | ደ/ብ/ህ/ክልል | ጌዴኦ ዞን | ዲላ |
| | | | ወናጎ |
| | | | ይርጋጨፌ |
| | | | ፍስሃገነት |
| | | | ኮቸሬ |
| | | | ጨለለቅቱ |

### 4.4. የመረጃ ምንጮችና የማስረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ይህንን ምርመራ በሚያካሂድበት ወቅት ግኝቶቹን ለማረጋገጥና ለማጠናከር በቀጥታ ከተጎጂዎችና ከተጎጂ ቤተሰቦች አቤቱታና ማስረጃ ተቀብሏል፤ ከምስክሮች የምስክርነት ቃል፣ ድርጊቱ በተፈፀመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ሁኔታውን በዓይን በማየትና በማጥናት፣ ከአካባቢው ነዋሪዎችም በመረዳት፣ በተጨማሪም የሠነድ፣ የፎቶግራፍና የቪዲዮ ማስረጃዎችን በመቀበል እና በመመርመር ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በተቻለበት ጊዜና ስፍራ ሁሉ ከመንግስት አካላት መረጃና ማስረጃ ተሰባስቧል፡

### 4.5. የምርመራ ስራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) አሁን የሚገኝበት በጣም ውሱን የሆነ የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የምርመራ ቁሳቁስ አቅም፣ ቀውሶቹ በሚጠይቁት ፍጥነት፣ መጠን፣ ስፋትና ድግግሞሽ ለመስራት አላስቻለውም። በሌሎችም አካባቢዎችና ሁኔታዎች ላይ እንደሚታየው ሁሉ እዚህም ተጎጂዎችና ቤተሰቦች እንዲሁም ምስክሮች በከፍተኛ ፍርሀት ውስጥ መሆንና በሚፈለገው መጠን ትብብር አለማድረጋቸው በዚህ የምርመራ ስራ ሂደት ወቅት ትልቅ ተግዳሮት ፈጥሯል። በመሆኑም የቀሩ ነገሮች ሊኖሩ ስለሚችሉ ወደፊት ሰፊና ዝርዝር ጥናት ለማድረግ እንዲቻል ሰመጉ ተጎጂዎችና ዜጎችን ጨምሮ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ ትብብር እንዲያደርጉለት በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ይጠይቃል።

## 5. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጉጂ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጌዴኦ ዞን በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ በሲዳማ እና ወላይታ ብሔረሰብ ተወላጆችና አባላት መካከል በተፈጠሩ ጥቃትና ግጭቶች ምክንያት የተፈፀሙ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች

### 5.1 በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ)

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል፡፡ የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል፡፡ ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፍገው አይገባም" ይላል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል፡፡ ኢትዮጵያም እነዚህን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የተቀበለች ሀገር እንደመሆኗ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት በሲዳማ ዞን እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምእራብ ጉጂ ዞን በሚገኙ በተለያዩ ቀበሌዎች ነዋሪ በነበሩ ዜጎች ላይ ግድያ ተፈጽሟል፡፡

በጌዲኦ ዞን የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር

1. **አቶ ዲቂቦ ጎበና፡-** ዕድሜ 40፣ ሥራ ገበሬ፣ በምዕራብ ገጁ ዞን በር በርኪርስ ኪጆኦ ወረዳ ሰብረቻ ቀበሌ ሚያዝያ 25 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 7:00 ሰዓት መሳሪያ የታጠቁ የጉጂ ተወላጆች መኖርያ ቤቱ ድረስ በመሄድ በጥይት ገድለውታል፡፡ ከታች በተራ ቁ. 2፣3 እና 4 የተገለጹት ባለቤቱና ሁለት ልጆቹም በመኖርያ ቤታቸው ተገድለዋል፡፡
2. **ወ/ሮ ብርቂ ደቂቦ፡-** ዕድሜ 35፣ ሥራ ገበሬ በምዕራብ ጉጂ ዞን በርቢርሣ ከጆኦ ወረዳ ሰኮርቻ ቀበሌ የሚኙ ደቂቦ ጎበና ባለቤት ሲሆኑ ሚያዝያ 25 ቀን 2010 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው ከባለቤታቸውና ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተገድለዋል፡፡ ቤታቸውም ተቃጥሏል፡፡
3. **ህፃን ብርሃኑ ደቂቦ፡-** ዕድሜ 8፣ በ25/8/10ዓ.ም አባቱ ተገድሎ መኖርያ ቤታቸውንም በእሳት ሲያቃጥሉት ከእናቱና ከህፃን እህቱ ጋር ህይወቱ አልፏል፡፡
4. **ህፃን አይነች ደቂቦ፡-** ዕድሜ 2፣ በ25/8/2010ዓ.ም አባቷ ተገድሎ ከእናቷና ከወንድሟ ጋር መኖርያ ቤታቸው ሲቃጠል ህይወቷ አልፏል፡፡
5. **አቶ ስኪኖ ሙላቱ፡-** ዕድሜ 55፣ ሥራ ገበሬ፣ ሀሩ ከተማ በ5/10/10 ዓ.ም በጌዶኦ ማህበረሰብ አባላት ጀርባው ላይ በጥይት ተመትቶ ሀላ ከተማ ጫካ ውስጥ አስክሬኑ ተገኝቶ በ6/10/10 ዓ.ም ከቀኑ 11:00 ሰዓት ሀራ ከተማ ደብረሰላም እግዚአብሔር ወልድ ቤተክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈፅሟል፡፡
6. **ወጣት ጨነቀ ግርማ ወልዴ፡-** ዕድሜ 23፣ ሥራ ነጋዴ፣ ሀሩ ከተማ ውስጥ በ03/10/10 ዓ.ም በጌዲኦ ወጣቶች በገጀራ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል፡፡
7. **ወጣት ቦኒሽ ገበየሁ ጥላሁን፡-** ዕድሜ 16፣ የቀን ሠራተኛ የነበረ በ3/10/10 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ሀሩ ከተማ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት አጠገብ የጌዲኦ ወጣቶች በዱላና በገጀራ ቀጥቅጠው ገድለውታል፡፡
8. **መ/ር ዓለሙ (የአባቱ ስም ያልታወቀ)፡-** ወደ ፎጌ መግቢያ ልዩ ቦታው ስድቻ አካባቢ በጌዲኦ ተወላጆች በጥይት ተገድሏል፡፡ በ28/10/10 ዓ.ም ኦሮሚያ ክልል ሻራ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ተፈፅሟል፡፡

**ሰንጠረዥ 2** በደቡብ ክልል በጌዲኦ ዞን ብሄርን መሰረት ያደረገ ጥቃት በገደብ፣ በኮቸሬ፣ በ7/ጨሎ እና በወናሳ ወረዳዎች በተቀሰቀሰበት ወቅት የተገደሉ ሰዎች ዝርዝር (የጌዶ ዞን ፖሊስ መምሪያ በሰጠው ማስረጃ መሰረት የቀረበ)

| ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | የተገደሉበት ቦታ | ወረዳ | ብሔር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አበራ ቃንቂ | ባንቆ ጣጣቱ | ገደብ | ጌዲኦ |
| 2 | ከበደ በቀለ ጉቴ | ›› | ›› | ›› |
| 3 | ሽፈራው በርሶ ባቢ | ›› | ›› | ›› |
| 4 | አሰፋ ታምሩ ቃንቂ | ›› | ›› | ›› |
| 5 | ህፃን ጡንሽ ሼጼ ቁኒ | ›› | ›› | ›› |
| 6 | ገግሶ ገልቶየ ዳማ | ጌልቻ | ›› | ›› |
| 7 | ወ/ሮ ንግስት ጨንቁ | ሀሎ ሀርጣሜ | ›› | ›› |
| 8 | አብረሃም ደያሶ | ›› | ›› | ›› |
| 9 | ወ/ሪት ሰናይት ሳሙኤል | ›› | ›› | ›› |
| 10 | በየነ መሐመድ | ›› | ከፋ | |
| 11 | ታደሶ ወደሶ | በነቆጉቲት | ›› | ›› |
| 12 | ክፍሌ ዱካ | ቀዱዳ | ይርጋጨፌ | ጌዲኦ |
| 13 | ፀጋዬ በዛብህ | ›› | ›› | ›› |
| 14 | ጨነቀ ገዳ | ›› | ›› | ›› |
| 15 | ግዛው ዱካሌ | › | ›› | ›› |
| 16 | ማርቆስ ሎሌ | ›› | ›› | ›› |
| 17 | ብርሃኑ ገጁ | ›› | ›› | ›› |
| 18 | ሀይሌ ሽንጦዬ | ሉኬ | ›› | ›› |
| 19 | ኤፍሬም ሹንጣ | ›› | ›› | ›› |
| 20 | ረጋሣ ኤርቢ | ›› | ›› | ›› |
| 21 | ማርያም መኮንን | ሐሩ | ›› | ›› |
| 22 | ሽብሩ በራቆ | ›› | ›› | ›› |
| 23 | ሽክኖ ሙላቱ | ›› | ›› | ›› |
| 24 | ክፍሌ አያና | ›› | ›› | ›› |
| 25 | ጥላሁን ካሱ | ጭርቁ | ›› | ›› |
| 26 | ሽዶ ዋሬ | ›› | ›› | ›› |
| 27 | ሆርዶፋ ጁቦ | ›› | ›› | ›› |
| 28 | ወ/ሮ ወርቂ ጂቦ | ›› | ›› | ›› |
| 29 | ማሞ ኡቴ | ›› | ›› | ›› |
| 30 | አለሙ ጁክሶ | ›› | ›› | ›› |
| 31 | መለሰ አለማ | ›› | ›› | ›› |
| 32 | ኤዲቱ ጎዲ | ›› | ›› | ›› |
| 33 | ንጉሴ ጎበና | ጭቶ | ይርጋጨፌ | ጊዲኦ |
| 34 | ዘውዴ ጋኒ | ዶማርሶ | ›› | ›› |
| 35 | አየለ ጠቀቦ | ›› | ›› | ›› |
| 36 | ገቱ መንገሻ | ›› | ›› | ›› |
| 37 | ገመደ ኢነዳ | ቱቲት ጨልባ | ›› | ›› |
| 38 | ደምሴ ባሊ | ራሊት | ›› | ›› |
| 39 | ቴኩ በቀለ | ሐ/ሀራንኘ | ›› | ›› |
| 40 | በዛብህ ህርማ | ቀዲዳ | ›› | ›› |
| 41 | ሙለዓለም ተስፋዬ | ›› | ›› | ›› |
| 42 | አዲሱ ህርባዬ | ባያ | ኮቸሬ | ›› |
| 43 | ታደሰ ህርባዬ | ›› | ›› | ›› |
| 44 | ሽፈራሁ ቡንጌ | ›› | ›› | ›› |
| 45 | ገመዴ ጅብቾ | ›› | ›› | ›› |
| 46 | ከበደ ቦጋለ | ›› | ›› | ›› |
| 47 | ዋቆ ዱቤ | ›› | ›› | ›› |
| 48 | ደስታ ገዲቻ | ›› | ›› | ›› |
| 49 | በርሶ ሄጤሳ | ›› | ›› | ›› |
| 50 | ግረማ ኤዶማ | ሀንጫቤ | ›› | ›› |
| 51 | ሽብሩ ቁጡዬ | ጀልዶ | ›› | ›› |

| ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | የተገደሉበት ቦታ | ወረዳ | ብሔር |
|---|---|---|---|---|
| 52 | በቀለ ሻሎ | ቢኖ | ›› | ›› |
| 53 | ሎምቤ ሻሎ | ›› | ›› | ›› |
| 54 | ኢበላ ጌሳ | ሀንጫቤ | ›› | ›› |
| 55 | እንዳልካቸው ካሳሁን | ቆሬ | ›› | ›› |
| 56 | ኢዮብ በየነ | ሽፎ | ›› | ›› |
| 57 | መርሹ አጠኔ | ›› | ›› | |
| 58 | ማርቆስ ዋቆ | ›› | ›› | ዲኦ |
| 59 | ገዛኸኝ ገመደ | ›› | ›› | ›› |
| 60 | ጀምበሩ ቦጋሌ | ›› | ›› | ›› |
| 61 | ልደቱ ተካልኝ | ሀንጫቤ | ›› | ›› |
| 62 | አብረሃም አባዬ | ገደብ | ›› | ›› |
| 63 | አየለ ሮቢ | ›› | ›› | ›› |
| 64 | አብረሃም እጅጉ | ›› | ›› | ›› |
| 65 | ተስፋዬ ገናሌ | ጨለለ ቅቱ | ›› | ›› |
| 66 | መንገሻ ወቴ | በንቆ ጣጣቱ | ›› | ›› |
| 67 | የሱፍ አርባ | ›› | ›› | ›› |
| 68 | መስፍን ዲያሶ | ›› | ›› | ›› |
| 69 | ተስፋዬ አለማየሁ | በ/ጋቲት | ›› | ›› |
| 70 | ከጅባ ሩፎ ወጅጋ | ›› | ›› | ›› |
| 71 | ወ/ሮ አልማዝ ማሮ | በ/ጨልመሌ | ›› | ›› |
| 72 | ታምራት ዲያሶ | ገ/ገልቻ | ›› | ›› |
| 73 | ኤፍሬም ጠቀቦ | ሀ/ባረት | ›› | ›› |
| 74 | ፍቃዱ ክፍሌ | በ/ጨልጨሌ | ›› | ›› |

**ሰንጠረዥ 3** በምዕራብ ጉጂ ዞን በጉጂና በጌዴኦ ብሔረሰቦች መካከል በተፈጠረው ግጭት ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎች ስም ዝርዝር (ከምዕራብ ጉጂ ዞን አስተዳደር ፅ/ቤት በተገኘ ማስረጃ መሰረት የቀረበ)

| ተቁ | የሟች ሙሉ ስም | ጾታ | አድራሻ | | ብሄር | | ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወረዳ | ቀበሌ | ኦሮሞ | ጌዲኦ | |
| 1 | ከፍያለው ፊጋ | ወንድ | ብ/ኮጆዋ | ደ/ኢዳራ | | ✓ | 04/08/10 |
| 2 | ጂሶ ጂቦ | ወንድ | ብ/ኮጆዋ | ደ/ሳኬ | | ✓ | 05/8/10 |
| 3 | ጠንጥራ ዱቤ | >> | ሀ/ዋም | ሀ/ሶርሳ | ✓ | | 06/08/10 |
| 4 | ከበደ ደስታ | >> | ሀ/ዋም | ተ/ጎዮ | ✓ | | 06/08/10 |
| 5 | ታሪኩ ብርሀኑ | >> | ሀ/ዋም | መ.01 | ✓ | | 06/08/10 |
| 6 | ንጋቱ ዋሬ | >> | ሀ/ዋም | ደ/ዋማና | ✓ | | 06/08/10 |
| 7 | አለማየሁ ወንዴ | >> | ሀ/ዋም | ዳሪ | | ✓ | 06/08/10 |
| 8 | ተስፋዬ አለሙ | >> | ቃርጫ | ሰ/ሳጳ | ✓ | | 03/08/10 |
| 9 | ሞርካ አባይ | >> | ቃሬጫ | መ.02 | ✓ | | 03/08/10 |
| 10 | ቱኔ ሎሌ | >> | ቃርጫ | ጎሮ | ✓ | | 06/08/10 |
| 11 | ኢርባ ጀጎ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ኦ/ሙዳ | | | |
| 12 | ማርያም | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ኦ/ሙዳ | | | |
| 13 | ደሳለኝ ዋቆ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ኦ/ሙዳ | | | |
| 14 | አሸናፊ ኦብሴ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ገርባ02 | ✓ | | |
| 15 | ገመቹ ጂሎ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ✓ | | |
| 16 | ዱቤ ቲሶ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ሀ/ሊፐ | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ክፍአለው ዱካሌ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | አ/ሙዳ | | | |
| 18 | ጂአ ጎንፎሎ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ቡሌ ሆራ | | | |
| 19 | ተስፋዬ ዋቆ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ቡሌ ሆራ | | | |
| 20 | ተስፋዬ ደያሶ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ቡሌ ሆራ | | | |
| 21 | በዴሳ ጃርሶ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ቡሌ ሆራ | | | |
| 22 | ስሙ ያልታወቀ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ቡሌ ሆራ | | | |
| 23 | ስሙ ያልታወቀ | ወንድ | ቀርጫ | ቀርጫ | | | |
| 24 | ክፍሌ ግርማ ሰሊ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ጉጂ | | |
| 25 | ሀሎ ታደሰ ኢሌቱ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ጉጂ | | |
| 26 | አዲሱ አብርሀም | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ጉጂ | | |
| 27 | ፍቃዱ ሙርቲ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ጉጂ | | |
| 28 | ሙሃባ አድማሱ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ጉጂ | | |
| 29 | ቱሬ በቀለ ዱቤ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | | ጉጂ | | |
| 30 | ገመደ በዳሳ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ዶ/ቡልቻ | | ጌዲኦ | |
| 31 | በዴሳ ቦራ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ዶ/ቡልቻ | | ጌዲኦ | |
| 32 | ስሙ ያልታወቀ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ገርባ 01 | | ጌዲኦ | |
| 33 | ስሙ ያልታወቀ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ገርባ 02 | | ጌዲኦ | |
| 34 | ስሙ ያልታወቀ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ሚጢቶም | | ጌዲኦ | |
| 35 | ደደቻ ቱዴ | ወንድ | ቀርጫ | ባንጎ ባያ | ጉጂ | | |
| 36 | ደስታ ዱቤ | ወንድ | ቀርጫ | ገሌሳ ቡርቃ | ጉጂ | | |
| 37 | ብርሀኑ ኑሬ | ወንድ | ቀርጫ | ሄራ ሊፒቱ | ጉጂ | | |
| 38 | በቀለ ዱቤ ሚጁ | ወንድ | ቀርጫ | ሄራ ሊፒቱ | ጉጂ | | |
| 39 | ደንቦቢ ጩቁላሳ | ወንድ | ቀርጫ | ገሌሳ/ዲቢሳ | ጉጂ | | |
| 40 | አራርሶ ጃኑ | ወንድ | ቀርጫ | ገሌሳ/ዲቢሳ | ጉጂ | | |
| 41 | ዱላቻ ባዳ | ወንድ | ቀርጫ | ኢጉ/አባዩ | ጉጂ | | |
| 42 | አብረሀም ታደሰ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 43 | ባሪሶ ጋዳቾ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 44 | ታዳለ ማሞ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 45 | ደቻሶ ዱቼ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 46 | ማንዳዮ ሮባ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 47 | አየለ ደቻሶ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 48 | ማሙሽ አለማዮ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 49 | አለሙ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 50 | ማሪያም መንገሻ | ወንድ | ቀርጫ | ላዮ/ቁንዲ | | ጌዲኦ | |
| 51 | ስሙ ያልታወቀ | ወንድ | ቀርጫ | ጪጋ ኪቢቻ | | ጌዲኦ | |
| 52 | ብርሀኑ ዘውዴ | ወንድ | ቀርጫ | ኢላ ፊርዳ | | ጌዲኦ | |
| 53 | ረጋሳ ዳያዮ | ወንድ | ቀርጫ | ኢላ ፊርዳ | | ጌዲኦ | |
| 54 | ጎሌ ብሬ | ወንድ | ቀርጫ | ኢላ ፊርዳ | | ጌዲኦ | |
| 55 | ጎበና (የአባቱ ስም ያልታወቀ) | ወንድ | ቀርጫ | ኢላ ፊርዳ | | ጌዲኦ | |
| 56 | ዋቆ ዱቤ | ወንድ | ገላና | በሪቲ | ጉጂ | | 27/9/10 |
| 57 | ፍቃዱ ፀጋዬ | ወንድ | ገላና | ጊዊ መጋላ | ጉጂ | | 29/9/10 |
| 58 | ጂአ አርቦ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 1/10/10 |
| 59 | ደረሶ ጎበና | ወንድ | ገላና | በሪቲ | ጉጂ | | |
| 60 | ሺፈራ ገባቻ | ወንድ | ገላና | አዳዶ | ጉጂ | | 19/10/10 |
| 61 | ዋሬ በዲዬ | ወንድ | ገላና | ሰፓሎ | ጉጂ | | 17/10/0 |
| 62 | ተስፋዬ ኢዴማ | ወንድ | ገላና | ቶሬ መጋላ | ጉጂ | | 26/9/10 |
| 63 | ዱካሌ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 64 | ኢሌማ ጢጣ | ወንድ | ገላና | ዋዶ ደርባ | ጉጂ | | |
| 65 | ጫና ኦዳ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 8/10/10 |
| 66 | አዶላ አዳሞ | ወንድ | ገላና | ቦሬ | ጉጂ | | 28/9/10 |
| 67 | ገመቹ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 68 | ገብሬ ጂሎ | ወንድ | ገላና | ጊዌ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 69 | ጎበና ቆራቱ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 70 | ኢሳቅ ቦኔ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 71 | ነጋዎ ዳቃቦ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 72 | ዱካሌ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 73 | ተስፋዬ ኢዴማ | ወንድ | ገላና | ቶሬ መጋላ | ጉጂ | | 26/9/10 |
| 74 | ዱካሌ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 75 | ኢሌማ ጢጣ | ወንድ | ገላና | ዋዶ ደርባ | ጉጂ | | |
| 76 | ጫና ኦዳ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 8/10/10 |
| 77 | አዶላ አዳሞ | ወንድ | ገላና | ቦሬ | ጉጂ | | 28/9/10 |
| 78 | ገመቹ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 79 | ገብሬ ጂሎ | ወንድ | ገላና | ጊዌ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 80 | ጎበና ቆራቱ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 81 | ኢሳቅ ቦኔ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 82 | ነጋዎ ዳቃቦ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 83 | ዱካሌ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 84 | ገመቹ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 85 | ገብሬ ጂሎ | ወንድ | ገላና | ጊዌ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 86 | ጎበና ቆራቱ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 87 | ኢሳቅ ቦኔ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 88 | ነጋዎ ዳቃቦ | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 89 | ዱካሌ ጎበና | ወንድ | ገላና | ሸሞሌ ሺዳ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 90 | ሳሮ ሮባ ዋጃጎ | ወንድ | መካ ሶዶ | ደ/ዲምቱ | | ጌዲኦ | 2/10/10 |
| 91 | ለገሰ ባቲ | ወንድ | ቡሌ ሆራ | ቆሬ | | ጌድኦ | 2/10/10 |
| 92 | ጌታቸው ሆርዶፋ ገመዴ | ወንድ | ሀንበላ | ቢርቢርሳ | | ጌዲኦ | 2/10/10 |
| 93 | ዳዊ ሮባ | ወንድ | ገደብ | ቆሬ | ጉጂ | | 2/10/10 |
| 94 | ክፍሌ ታምራት አርባ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | ጨርሶ ጎርጃ | | ጉጂ | 28/09/10 |
| 95 | ግርማ አበበ መርከቡ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | ጨርሶ ጎርጃ | | ጉጂ | 28/09/2010 |
| 96 | ሳሙኤል ሳሊ ዋቆ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | ደሪ ግዳሜ | | ጌዲኦ | 27/09/2010 |
| 97 | ዋያ ሎሌ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | ጨርሶ ጎልጃ | | ጌዲኦ | 27/09/2010 |
| 98 | ዋሬ ዱቤ ዳሮ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | | ጉጂ | | |
| 99 | አየለ ተፈራ ጉቺ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | | ጉጂ | | |
| 100 | ቱሬ ደለቻ ዋዩ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | ቡሌ ሀንበላ | ጉጂ | | |
| 101 | ታምሩ ጃቦ ሳሊ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | | | ጌዲኦ | |
| 102 | ንጋቱ ዋሬ ሮቤ | ወንድ | ሀንበላ ዋማና | | | ጌዲኦ | |
| 103 | ኡዴሳ ዱቤ ዋጤ | ወንድ | ብ/ኮጃዋ | | ጉጂ | | |

### 5.2 የአካል ጉዳት፡- በጥይት ማቁሰልና ድብደባ

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 18(1) ‹‹ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢ- ሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው›› ተብሎ የተደነገገውንና በዓለም አቀፉ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 5 ‹‹ማንም ሰው የማሠቃየት ድርጊት ሊፈጸምበት ወይም በጭካኔና ኢ ሰብዓዊ በሆነ መንገድ ሊጉላላ ወይም ሊዋረድ አይችልም ወይም ሊቀጣ አይችልም›› እንዲሁም ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የአፍሪካ የሰዎችና ህዝቦች መብት ቻርተር አንቀፅ 5 እና 6 ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብር ያለው በመሆኑ ያላግባብ እንደማይታሰር፣ እንግልትና የማሰቃየት ድርጊት እንዳይፈፀምበት ይከለክላል፡፡

ኢትዮጵያ ተቀብላ የፈረመችው ማሰቃየትን፣ ሌሎች ጭካኔ የተሞላባቸው፣ ሰብዓዊነት የጎደላቸውና አዋራጅ የሆኑ አያያዞችንና ቅጣቶችን ለማስቀረት በተደረገው ስምምነት ክፍል አንድ አንቀፅ 2 እያንዳንዱ ይህንን ስምምነት የተቀበለ ሀገር በግዛት ክልሉ ውስጥ በዜጎቹ ላይ በማናቸውም ሁኔታ የማሰቃየት ድርጊት መፈፀም እንደሌለበትና ይህንንም መከላከል እንዳለበት ስምምነቱን በፈረሙ ሀገራት ላይ ግዴታ ይጥላል፡፡ ነገር ግን እነዚህን ስምምነቶችና በህግ የተደነገገውን በመጣስ ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሱት ሰዎች ላይ ድብደባና ማሠቃየት ተፈጽሟል፡፡

**ሰንጠረዥ 4** በደቡብ ክልል በጌዲኦ ዞን በተለያዩ ወረዳዎችና በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ጉጂ ዞን በአዋሳኝ ድንበር አካባቢ በተፈጠረ ግጭት የአካል ጉዳት የደረሰባቸው (ከቡሌ ሆራ ሆስፒታል በተገኘ ማስረጃ መሰረት)

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ጉዳቱ የተፈፀመበት ቦታ | የጉዳት መጠን | ብሔር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አብረሃም በደቻ | ሀ/ባረት | ከፍተኛ ጉዳት | ጌዲኦ |
| 2 | አየለ በሬሳ | ሀርሙፎ | ›› | ›› |
| 3 | ነጋ ሳሙኤል | | ›› | |
| 4 | ጌቱ ባሊ በራቆ | ኤደራ | ›› | ጌዲኦ |
| 5 | ወ/ሮ ፍሬነሽ ፊጋ | ›› | ›› | ›› |
| 6 | ወ/ሮ አበበች ማሞ ኩርሴ | ›› | ›› | ›› |
| 7 | አቶ ገብሩ ኃ/ማርያም | ›› | ›› | ›› |
| 8 | ግዛቸው እያሱ ዳንኤል | በ/ጣጣቱ | ›› | ›› |
| 9 | ኤፍሬም ሽብሩ | ገደብ | ›› | ›› |
| 10 | አቶ አብረሃም | ›› | ›› | ›› |
| 11 | ገልገሌ ሻንቆ በርሶ | ›› | ›› | ›› |
| 12 | ሚካኤል ተሰማ | ›› | ›› | ›› |
| 13 | ኡዳ ጂሎ | ቡሌ ሆራ | ›› | ›› |
| 14 | ጨሌ ከበደ | ቡሌ ሆራ | ›› | ›› |
| 15 | ሉኦ አጋ | ቡሌ ሆራ | ›› | ›› |
| 16 | ሜጣ ሆጤሳ | ሀንበላ ዋማና | ›› | ›› |
| 17 | ሺብሩ ቦናያ በሪሶ | ሀንበላ ዋማና | ›› | ጉጂ |
| 18 | ግዛው ዳንጎ | | ›› | ጌዲኦ |
| 19 | ዳዊት ሻሎ | | ›› | ጌዲኦ |
| 20 | መኮንን ሞና | >> | | ኦሮሞ |
| 21 | ቱኬ ሂርባዬ | >> | | ኦሮሞ |
| 22 | ማቲዎስ (ያባቱስም ያልታወቀ) | | | ኦሮሞ |
| 23 | አየለ ጂሎ | | | ኦሮሞ |

**ሰንጠረዥ 5** በሀዋሳ ከተማ ከጨንበላላ በዓል ጋር ተያይዞ በሲዳማ ብሄር ተወላጆች በከተማውና አካባቢው በሚኖሩ የወላይታ ተወላጆች ላይ በተፈጸመ ጥቃት ከሰኔ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በሃዋሳ ከተማና ዙሪያዋ በተከሰተ ግጭት ምክንያት ህይወታቸውን ያጡ ዜጎች (ከአዳሬ ሆስፒታል በተገኘ ማስረጃ መሰረት)

| ተ.ቁ | ስም ከነአባት | ዕድሜ | ጾታ | የጉዳቱ ምክንያት | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰለሞን አብዮ | 50 | ወ | | ሀዋሳ ከተማ ጫፌ ሰፈር |
| 2 | ታደመ ቢታና | 50 | ወ | በዱላ ተደብድቦ | ሃዋሳ ከ.ታቦር |
| 3 | ሺመልስ ሺብሩ | 30 | ወ | በድንጋይና በዱላ ተደብድቦ | ሃዋሳ ሀይቅ ዳር |
| 4 | ሳጅን ዘሪሁን ዛና | 52 | ወ | | ሀዋሳ ታቦር |
| 5 | ትግሉ ተሰፋዬ ጫላ | 20 | ወ | በጥይት | ሃዋሳ ታቦር |
| 6 | በለጠ ጎዳሮ | | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 7 | ብዙአየሁከበደ | 29 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 8 | ምትኩ ያዳያያ | 30 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 9 | ተፈራ አሸናፊ ጨቦ | 30 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 10 | አክሊሉ ቱሻ ደቦዬ | 26 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 11 | ሰለሞን ይመርአሱ | 27 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 12 | ሙላቱ ወልዴ | 27 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 13 | ደሳለኝ ዳዊት | 30 | ወ | | ሃዋሳ ታቦር |
| 14 | ዲጋ ሰርባሞ | 55 | ወ | | ሉንቡሎ ቃጅሞ |
| 15 | ርቅዋዩ ቱራ | 60 | ወ | | ሉንቡሎ |
| 16 | ንጉ ሴጀጆ | 40 | ወ | | ላቡ ኮሮሞ |
| 17 | ቡሴ ኢዩኤል | 41 | ወ | | ሽመና ሁሩፋ |
| 18 | ሳንጃ ጋማዳ | 20 | ወ | | ባኬ ላሊማ |

በሀዋሳ ከተማ ከጨንበለላ በዓል ጋር ተያይዞ በሲዳማ ብሄር ተወላጆች በከተማውና አካባቢው በሚኖሩ የወላይታ ተወላጆች ላይ በተፈጸመ ጥቃት ከሰኔ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በሃዋሳ ከተማና ዙሪያዋ በተከሰተ ግጭት ምክንያት ሕይወታቸውን ያጡ ዜጎች ፎቶግራፍ፡፡



መሀመድ አንዛ



ሙላቱ ኩማ



ታመረ ጨርቆ



ዘሪሁን ዜና



በለጠ ጎድሮ

**ማስታወሻ፡**

አንድ ሰው በወቅቱ ሞቶ አስከሬኑ ያልተገኘ መሆኑን ከሲዳማ ዞን ፖሊስ የተገኘ ሰነድ ያስረዳል፡፡ ስማቸው ያልታወቀ 2 ወንዶች እና 1 ሴት በግጭቱ ወቅት በደረሰባቸው ጉዳት ሆስፒታል ገብተው መሞታቸውን ከሆስፒታል የተገኘ ሰነድ ያስረዳል፡፡

**ሰንጠረዥ 6 በግጭቱ ወቅት የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር**

| ተቁ | ስም | ፆታ | የደረሰ ጉዳት | የጉዳቱ ምክንያት | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ዘለቀ በዙ ባቾሬ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በድንጋይና በዱላ ድብደባ | ሃዋሳ ታቦር |
| 2 | ማስረሻ ግዛዉ ኀበና | ወ | ቀላል የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሃዋሳ ታቦር |
| 3 | እፋዉ በዛብህ ቦዳ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሃዋሳ ታቦር |
| 4 | ዘሪሁን አዱኛ ወኒ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በድንጋይና በዱላ ድብደባ | ሀዋሳታቦር |
| 5 | ሹፌ ሁሴን ሰኢድ | ወ | ቀላል የአካል ጉዳት | | ሃዋሳ ታቦር |
| 6 | ምኪያስ ኦታንሳቱሉ | ወ | ቀላል የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 7 | አበበ ሽዋ ወንዴ | ወ | ቀላል የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሃዋሳ ታቦር |
| 8 | በላይ አበራ ዳምጤ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በድንጋይና በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 9 | አሸብር ጥላሁን ደጉ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በድንጋይና በዱላ ድብደባ | ሃዋሳታቦር |
| 10 | አስራት አሊፎከጀላ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሃዋሳ ታቦር |
| 11 | ተስፋዬጋንታ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ቱላ |
| 12 | ቡዋ ቡሬቃ ጋንገሶ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | በድንጋይ ድብደባ | ወንዶ ገነት |
| 13 | መልካሙ ተሸለ ከትሶ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | | ሀዋሳ ታቦር |
| 14 | ሰለሞን ወና | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | | ሀዋሳ ታቦር |
| 15 | ተሰማ ተገኝ | ወ | ከባድ የአካል ጉዳት | | ሀዋሳ ታቦር |
| 16 | አበባየሁ አሸናፊ | ወ | ቀላል የአካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 17 | ሽጋዉ አንተነዉ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 18 | ሕዝቅኤል ቦሻለ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ወንዶ ገነት |
| 19 | አናኖ ቶቻሞ ሓይሳ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሻመና |
| 20 | ገዛሄኝ ባነሮ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላድብደባ | ሀዋሳ |
| 21 | ብረሃኑ ጋቢሶ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላድብደባ | ወንዶገነት |
| 22 | በረከት ባንጫ ዱላ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላድብደባ | ሀዋሳ |
| 23 | ደረጀ ያዉሬ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላድብደባ | ሀዋሳ |
| 24 | ሰለሞን ከበደ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላድብደባ | ሀዋሳ |
| 25 | ዳዊትበሮዶሀንካሞ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | | ሀዋሳ |
| 26 | አዱኛ ሲናቶ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 27 | አበዱዋሰ አህመድ አሊ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋይ ድብደባ | ሃዋሳ |
| 28 | ብርሃኑ ጴጥሮስ ቡሾ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 29 | መኢቦ መንድሮ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 30 | ብርሀኑ ዳታሞ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ደረባፋና(02) |
| 31 | ኤሊያስ ኀበና | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሸበዲኖ |
| 32 | መልካሙ ደበሎ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋይ ተመትቶ | ሀዋሳ ታቦር |
| 33 | ጌታሁን በሮዳ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 34 | ብሩክ ምከሩ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | | ሀዋሳ ታቦር |
| 35 | ሰእር መንግስቱ | ሴ | ቀላል አካል ጉዳት | | ሀዋሳ |
| 36 | እጅጉ ሻንቆ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በድንጋይና ዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 37 | ዮሃንስ ዮንኩራ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋይ ተመትቶ | ሸበዲኖ |
| 38 | ወንድሙ አበራ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሸበዲኖ |
| 39 | ኩማ ረጋሳ ጨኔቀ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 40 | ብርሃኑ ስዩም ገ/ወ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሀዋሳ መናሄሪያ |
| 41 | ተከተ ልግአ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ዳቶ |
| 42 | ሀግረሶካባ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በድንጋይና ዱላድብደባ | ሀዋሳ ዳቶ |
| 43 | ሀሚሳር አብራር | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በቦክስ | ሀዋሳ ታቦር |
| 44 | ላቶገዳሞ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድነጋይ ተመትቶ | ሀዋሳ ታቦር |
| 45 | ሹሩብቱ አብረሀም | ሴ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ቱላ |

| ተቁ | ስም | ፆታ | የደረሰ ጉዳት | የጉዳቱ ምክንያት | አድራሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| 46 | አብረሃም ባሙድ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 47 | ሚኪያስ አንጎሳ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላድ ብደባ | ሀዋሰ ታቦር |
| 48 | ቢኒም ሞላ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋይ ተመትቶ | ሀዋሳ ( ዩኒቨርሲቲ ዋናው ጊቢ) |
| 49 | ይስሓቅ ከመች | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | ድንጋይ | ሃዋሳ ታቦር |
| 50 | ያሬድ አቢይ ሙላት | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 51 | ቡእራ ቦዳ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሀዋሳዶሬ |
| 52 | ቀመሪያ አወል | ሴ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሀዋሳ ታቦር |
| 53 | ዘካሪያስ ዛዛ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በድንጋይ ተመትቶ | ሀዋሳ ታቦር |
| 54 | ሳሙኤል ወንዶ | | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሃዋሳ |
| 55 | ቢኒያም ሄኖክ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በድንጋይ ተመትቶ | ሀዋሳ ቱላ |
| 56 | አድማሱ ማንደዶ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በድንጋይና በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 57 | ትዕዛዙ በቆዬ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋይ ተደብድቦ | ሀዋሳ |
| 58 | አብዱረዛቅ ኢብራሂም | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋይ ተደብድቦ | ሀዋሳ |
| 59 | አንፍሬ ዘሪሁን | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድነጋይ ተመትቶ | ሀዋሳ |
| 60 | ፈለቀ ጩኮ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ ታቦር |
| 61 | በራሬ ርክቤ | ወ | ከበድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሃዋሳ |
| 62 | ናሆም(የአባትስምያልታወቀ) | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 63 | አየለ አመሎ | ወ | ቀላል አካል ጉዳት | በድንጋ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 64 | ታሪኳ ዋዱባለ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | ሀዋሳ ታቦር |
| 65 | መብራቱ ሆሎም | ሴ | ቀላል አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |
| 66 | ቱመራ ተፈራ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በጥይት | |
| 67 | ሙሌ አስቻለዉ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በድንጋይ ድብደባ | ሀዋሳ ቱላ |
| 68 | አበበ ሸዋ | ወ | ከባድ አካል ጉዳት | በዱላ ድብደባ | ሀዋሳ |

ከላይ ከተዘረዘረው በተጨማሪ ከሀዋሳ ከተማ አስተዳደር አዳሬ ሆስፒታል የተገኘ ሰነድ እንደሚያስረዳው ከፍቼ ጨንበለላ በዓል ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ብጥብጥ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ወደ ሆስፒታሉ ገብተው ታክመው የወጡ 6 ሴቶችና 23 ወንዶች መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 5.3 ማፈናቀልና ንብረት ማውደም

### ማፈናቀል

**ሰንጠረዥ** 7 ጌዲኦ ዞን ተፈናቃዮች አጠቃላይ የተፈናቃይ ቁጥር እስከ 25/10/2010 ዓ.ም

| ተ.ቁ | ወረዳ | አባወራና እማወራ | | | በቤተሰብ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አባወራ | እማወራ | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| 1 | ገደብ | 37,707 | 15,366 | 53073 | 201,719 | 187,927 | 389,646 |
| 2 | ቡሌ | 8,113 | 682 | 8,795 | 27,983 | 28,500 | 56,483 |
| 3 | ኮቾሬ | 13,66 | 3,933 | 17,594 | 50,982 | 52,281 | 103,263 |
| 4 | ወናጎ | 5,535 | 1,053 | 6,588 | 26,196 | 24,156 | 50,352 |
| 5 | ይ/ጨፌ | 19,801 | 5,140 | 24,941 | 90,094 | 85,486 | 175,580 |
| 6 | ዲላ ዙሪያ | 2,601 | 747 | 3,348 | 11,050 | 11,171 | 22,221 |
| 7 | ዲላ ከተማ | 7,627 | 2,162 | 9,789 | 32,005 | 30,506 | 62,511 |
| | **ድምር** | **95,045** | **29,083** | **124,128** | **440,029** | **420,027** | **860,056** |

## ንብረት ማውደም

**ሰንጠረዥ 8** ከሀዋሳ ከተማ የተፈናቀሉ ሰዎች ብዛትና የተጠለሉባቸው ቦታዎች ዝርዝር

| ተ.ቀ | ተጠልለው የነበሩበት ቦታ | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ታቦር 1ኛ ት/ቤት | 1575 |
| 2 | እድገት ፋና ት/ቤት | 3030 |
| 3 | እርዳታ ማስተባበሪያ ሲሳሴ | 700 |
| 4 | አዲስ ከተማ ት/ቤት | 4500 |
| 5 | ሀይቅ 1ኛ ት/ቤት | 3000 |
| 6 | አዲሱ ስቴዲዮም | 180 |
| 7 | አተዮጵያ ትቅደም | 1500 |
| **ድምር** | | **14,485** |

**ሰንጠረዥ 9** በ8/10/2010 ዓ.ም በሶዶ ከተማ የመልካም አስተዳደር ጥያቄ ጋር ተያይዞ በተደረገ ሰላማዊ ሰልፍ ወቅት ኮንቴነር ሱቆች ውስጥ በመነገድ የሚተዳደሩ የጉራጌ ብሄር ተወላጆች ንብረት በሆኑ ሱቆች ላይ ሰልፈኞቹ ከፍተኛ የንብረት ማውደም አደጋ አድርሰዋል፡፡ ተጎጂዎች ለወላይታ ዞን አስተዳደር የወደመባቸውን ንብረት ግምት በአቤቱታቸው ላይ በገለፁት መሰረት፡፡

ንብረት ላይ የደረሰ ጉዳት ፡-

| ተቁ. | የባለ ንብረቱ ስም | የወደመ ንብረት በብር |
|---|---|---|
| 1 | መዘምል ጀማል | 350,000.00 |
| 2 | ታደለ ዳዊ | 465,000.00 |
| 3 | ትዕግስቱ ሽኩር | 450,000.00 |
| 4 | አሰፋ አንጀሎ | 520,000.00 |
| 5 | አዲስዓለም ዘዉገ | 480,000.00 |
| 6 | በቀለ አቅንዳ | 550,000.00 |
| 7 | አዳነ ዳዊ | 230,000.00 |
| 8 | ፀጋዬ ክብሩ | 500,000.00 |
| 9 | መሐመድ ግራኝ | 540,000.00 |
| 10 | ክንፈ ግርማ | 300,000.00 |
| 11 | ፈለቀ ሀይሌ | 450,000.00 |

| ተቁ. | የባለ ንብረቱ ስም | የወደመ ንብረት በብር |
|---|---|---|
| 12 | ማርታ | 305,000.00 |
| 13 | ነኛ ኑረዲን | 520,000.00 |
| 14 | ሳሳ ደሊል | 100,000.00 |
| 15 | ታከለ ባሳ | 160,000.00 |
| 16 | ኡስማን መሀመድ | 250,000.00 |
| 17 | ታዲዎስ ሻንካ | 150,000.00 |
| 18 | ጠቀልል ፍቅሬ | 550,000.00 |
| 19 | አበራሽ ፈቃዱ | 450,000.00 |
| 20 | ከረዲን ጀማል | 550,000.00 |
| 21 | ጌታሁን ሀይሌ | 650,000.00 |
| 22 | እንዳለ ለጋ | 550,000.00 |

**ጠቅላላ ድምር በአቤቱታ አቅራቢዎች ግምት መሰረት ፡ብር 13,805,000.00 (አስራ ሶስት ሚሊዮን ስምንት መቶ አምስት ሺህ ብር)**

በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በወላይታ ዞን በሶዶ ከተማና በሁምቦ ከተማ ወጣቶች የተቃውሞ ሰልፍ በማድረግ የተለያዩ ጥፋቶችን በማድረሳቸው ሁምቦ ወረዳ የሚኖሩ፣ በከብት እርባታ የሚተዳደሩ የሲዳማ ተወላጆች በሥጋት ብዛታቸው 1,224 የሚሆኑ ከብቶቻቸውን ይዘው ወደ ሲዳማ ዞን አባያሎካ አባያ ዙሪያ ወረዳ ተፈናቅለው መምጣታቸውን የሰመጉ ባለሙያዎች የአባያሎካ ወረዳ አስተዳዳሪን በማነጋገር አረጋግጠዋል፡፡ በችግሩ ላይ ከሁምቦ ወረዳ አስተዳዳሪ ጋር ውይይት መደረጉንና ተፈናቃዮች ወደ ነበሩበት እንዲመለሱ ለማድረግ ስምምነት ላይ መደረሱን ገልጸዋል፡፡

**ከጨምበላላ በዓል ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ሁከት በሲዳማ ወጣቶች የተፈፀመ የንብረት ጉዳት**

1. ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 3 ሰዓት በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ጢልቴ ቀበሌ ወደሚገኘው አቤኔዘር የቤትና የቢሮ እቃዎች ድርጅት የሄዱ 50 የሚሆኑ ወጣቶች የተለያዩ ማሽነሪዎችን የእንጨትና የብረት፣ ጥሬ እቃዎችን፣ የተመረቱ እቃዎችን አጠቃላይ ግምቱ 3,615,000.000 ብር የሚሆን ንብረት በዝርፍያ መውሰዳቸውን የድርጅቱ ባለቤት ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
2. ሰኔ 08 ቀን 2010 ዓ.ም ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ጢልቴ ቀበሌ ነዋሪ ወደሆኑት አቶ አድማሱ ባፋ የሄዱ ከ70 በላይ የሚሆኑ ወጣቶች የቤት ንብረታቸውን እንደዘረፏቸው፣ መስኮትና በር ነቅለው እንደሰዱባቸው፣ በአጠቃላይ ግምቱ 500,000.000 ብር የሚገመት ንብረት የተዘረፈባቸው መሆኑን ተጎጂው ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
3. ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰዓት በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ሂጣታ ቀበሌ በሚገኘው የአቶ ታሪኩ ቡናሮ መኖሪያ ቤትና የንግድ ድርጅት ላይ የተደራጁ ወጣቶች ዘረፋ በመፈጸምና በማውደም ግምቱ 2,500,000.00 የሆነ የንብረት ጉዳት እንዳደረሱባቸው ተጎጂው ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
4. ከሰኔ 7 እስከ 9 ቀን 2010 ዓ.ም ድረስ በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ የሚገኘውን የአቶ አለማየሁ መኩሪያ የግል መኖሪያ ቤት የተደራጁ ወጣቶች በመስበር የቤት እቃዎችን፣ የቤት መዝጊያና መስኮት ነቅለው በመውሰድ ግምቱ ከ2,500,000.00 - 3,000,000.000 ብር የሚገመት የንብረት ጉዳት ያደረሱባቸው መሆኑን ተጎጂው ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
5. ሰኔ 7 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት በሀዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ሒጠታ ቀበሌ በሚገኝ ሰሌሆም መካከለኛ ክሊኒክ ላይ ጥቃት የፈጸሙ 20 የሚሆኑ የተደራጁ ወጣቶች የህንጻውን ሙሉ አልሙንየምና መስታወት መሰባበራቸውን፣ የህክምና ማሽኖችንና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን ማውደማቸውን፣ በአጠቃላይ ግምቱ 1.2 ሚሊዮን ብር የሚሆን ጉዳት ማድረሳቸውን አቶ አስራት ሞጆ የክሊኒኩ ስራ አስኪያጅ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
6. በሲዳማ ዞን በይርጋለም ከተማ በሰኔ 8 ቀን 2010 ዓ.ም በተፈጠረ የፀጥታ ችግር ምክንያት ንብረት የተዘረፈባቸው የሌሎች ብሄር ተወላጅ ነጋዴዎች በንግድ ማህበር ምክር ቤት የተጣሩት የ56 ነጋዴዎች ንብረት 10,821,695 የሚገመት ንብረት በሲዳማ ወጣቶች ተዘርፏል፡፡
7. በ07/10/2010 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ገደማ በአዋሳ ከተማ ታቦር ክፍለ ከተማ ሂጠታ ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው ሳሊሆም መካከለኛ ክሊኒክ ላይ በተፈጸመ ጥቃት ግምቱ 1.2 ሚሊዮን ብር የሚሆን ጉዳት በሕንፃውና በንብረቶች ላይ መድረሱን፣ የህክምና መሳሪያዎች መውደማቸውን የድርጅቱ ስራ አስኪያጅ ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
8. **በአዋሳ ከተማ** ዱሜ ቀበሌ ሰኔ 9 ቀን 2010 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት አብርሃም አየለ ባርና ሬስቶራንት ድርጅት ላይ በመስታዎት የተሰራውን ክፍል በመሰባበር፣ ፍሪጆችን፣ ጠርሙሶችንና የቤቱን መስታወት በመሰባበር ግምቱ 2,500,000 ብር የሆነ የንብረት ጉዳት መድረሱን የድርጅቱ ባለቤት ለሰመጉ አመልክተዋል፡፡
9. **በሲዳማ ዞን ወንዶ ገነት ወረዳ** በሶስት ቀበሌዎች ጩኮ 01፣ ኬላ 01፣ ወሻ ሶያማ ቀበሌ ነዋሪዎች የሆኑ የወላይታ ማህበረሰብ ተወላጆች መኖሪያ ቤቶች በሲዳማ ወጣቶች በእሳት የተቃጠለባቸውና ንብረታቸው የወደመባቸው ሲሆን በተጨማሪም በወሻ ቀበሌ ሰኔ 8 እና 9 2010 ዓ.ም፡-
    - 10 ቤቶች ከነሙሉ ንብረታቸዉ ወድመዋል
    - 32 ቤት በከፊል የወደመ ሲሆን በውስጡ ያለው ንብረት ሙሉ በሙሉ ተዘርፏል
    - አንድ ት/ቤት በሙሉ የቢሮ ዕቃዎች ኮመፒተሮችና መጽሀፍቶች ወድመዋል
    - 5 ሱቆች ከነሙሉ ሸቀጣቸዉ ወድመዋል
    - 4 እድሮች ሙሉ ዕቃቸው ወድሟል በአጠቃላይ በዚህ ቀበሌ ግምቱ 5,598,068 የሚገመት ንብረት ጉዳት ደርሶበታል

- ጩኮ 01 ቀበሌ 231 ወንድ 265 ሴት በድምሩ 496
- ኬላ 01 ቀበሌ 86 ወንድ 91 ሴት በድምሩ 177
- ወሻ ሶየሳ ቀበሌ 125 ወንድ 158 ሴት በድምሩ 283 የቤተሰብ አባላት ላይ የንብረት ጉዳት ደርሷል

በአጠቃላይ በመግለጫው ውስጥ የተዘረዘሩትን የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለማስቆም የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞንና የወረዳ የመንግሥት አካላትና የጸጥታ መዋቅሮች በተለይም ግጭቶችን ቅድመ መከላከልና ድርጊቱም ሲፈፀም ፈጥኖ በመድረስ ማስቆም ሲችሉ ይህንን ባለማድረጋቸው ጉዳቱ ከፍተኛ ጥፋት ሊያስከትል ችሏል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ የአስተዳደር አካላትና የፀጥታ ሀይሎች በግጭቱ ላይ እጃቸው እንዳለበት ተጎጂዎች ለሰመጉ ገልፀዋል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

የሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት ብሄር ተኮር የሆኑ ጥቃቶችና ግጭቶች በክልሎች፣ በዞኖችና በወረዳዎች በሚኖሩ ዜጎች መካከል ሲቀሰቀሱና የበርካታ ወገኖችን ህይወትና ንብረት ሲያጠፉ እንደነበር ይህም ጉዳይ በቂ ትኩረትና ዘለቄታዊ ህጋዊ መፍትሄ እንዲሰጠው በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌደራል እርከን ለሚገኙ የመንግስት አካላት ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

በዚህ 146ኛ ልዩ መግለጫ መግቢያ ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የተከሰተው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ከወትሮ በተለየ ሁኔታ በተመሳሳይ ወቅት ሰፊ አካባቢን የሸፈኑ ብሄር ተኮር ግጭትና ጥቃቶች ማለትም በኦሮሚያ ክልል በምዕራብ ጉጂና ምስራቅ ጉጂ ዞኖች፤ እንዲሁም በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በሲዳማ፤ በጌዲኦና በወላይታ ዞኖች ውስጥ በስፋት ተከስተው በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሞት፤ የአካል ጉዳት፤ መፈናቀልና የንብረት ውድመት ደርሷል፡፡ ብሄር ተኮር ለሆኑ ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት በመስጠት ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች በእውነተኛነት በማድመጥ ለግጭቶቹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑትን ምንጮች በማጥናት፣ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ እርምጃዎችን በመውሰድ በጥቃቱና በግጭቱ እጃቸው ያለበት አካላትን ተጠያቂ በማድረግ፣ ዜጎችን በሀገራቸው በእኩልነትና በሰላም በፍለጉት ቦታ የፈለጉትን ስራ ሰርተው የመኖር ህገ መንግስታዊ መብታቸው ተከብሮ እንዲኖሩ መንግስት ጥረት እያደረገ ቢሆንም በይበልጥ ችግሮች ከመከሰታቸውና የሰው ህይወት ጠፍቶ የአካል ጉዳትና ንብረት ውድመት ከማስከተላቸው በፊት በቂና አስተማማኝ፤ ተቋማዊና ዘላቂ የሆነ ለዜጎች ዋስትና የመሆን እርምጃ መወሰድ ላይ ገና ብዙ ይቀረናል፡፡ አሁንም በዚህ ድርጊት እጆቻቸውን የከተቱ አካላትም ጉዳዩ በማስረጃ ተጣርቶ ለህግ መቅረብ እና ተጎጅዎችና የተጎጂ ቤተሰቦችም ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙ በመንግስት በኩል ብዙ ይጠበቃል፡፡

በዚህ መገለጫ ላይ የተካተቱት የሞት፤ የአካል ጉዳት ማስረጃዎች የተገኙት ከሆስፒታሎች፤ ከፖሊስ ጽ/ቤቶች፤ ከተጎጂ ቤተሰብና የዓይን ምስክሮች ሲሆን የመፈናቀልና፤ የንብረት ውድመትን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ከየዞኖቹ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት መ/ቤቶች፤ ከአስተዳደር ጽ/ቤቶች፤ ከፖሊስ ጽ/ቤቶች፤ ከተጎጂዎች፤ ከተጎጂ ቤተሰቦችና የዓይን ምስክሮች ነው፡፡

በተለይ በመፈናቀሉ ወቅት ተጎጂዎችና ቤተሰቦቻቸው ሰነዶቻቸው የወደሙባቸው በመሆኑ የሚኞችን ፎቶግራፍና ተጓዳኝ ማስረጃዎችንና ሰነዶችን ለማግኘት አስቸጋሪ ከማድረጉም በላይ የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች ስለደረሰው የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ማስረጃ እንዲሰጡ የቀረበላቸውን ጥያቄ ለመቀበል ጥቂቶች ፍቃደኛ ቢሆኑም አብዛኞች መ/ቤቶች ግን የተጠየቁትን ማስረጃ ለመስጠት ዳተኝነት ታይቶባቸዋል፡፡ ማስረጃ በመስጠት ረገድ በርካታ የመንግስት ተቋማት ኃላፊነታቸውን በመወጣት ላይ ብዙ ይቀራቸዋል፡፡

ስለሆነም የተጎጂዎች ቤተሰቦች፣ ተጎጂዎች፣ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት፣ እንዲሁም ለሰብዓዊ መብት መከበር የምትቆረቆሩ ዜጎች ሁሉ መረጃዎችንና ማስረጃዎችን ለሰመጉ እንዲደርስ በማድረግ የበኩላችሁን ድጋፍ በማድረግ የዜግነትና የሰብዓዊነት ግዴታችሁን እንድትወጡ ሰመጉ በአክብሮት ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## 7. ማሳሰቢያ

በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ዜጎች ለሚያነሷቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ተገቢ የሆነ ምላሽ መንግስት ባለመስጠቱ ምክንያት የተለያዩ ተቃውሞዎች በመቀሰቀሳቸውና በመነሳታቸው ለበርካታ ዜጎች ህይወት መጥፋት፣ መቁሰል፣ መታሰርና ለከፍተኛ የንብረት መውደም ምክንያት ሆኗል፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ሰመጉ) ይህ ጉዳይ በቂ ትኩረትና ዘለቄታዊ ህጋዊ መፍትሄ እንዲሰጠው በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌደራል እርከን ለሚገኙ የመንግስት አካላት ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

አሁንም በዚህ 146ኛ ልዩ መግለጫው መንግስት ህብረተሰቡ የሚያነሳቸውን ጥያቄዎች በቂ ትኩረት በመስጠትና በማዳመጥ፣ ለግጭቶቹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑትን ምንጮች በማጥናት፣ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ እርምጃዎችን በመውሰድ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ እጃቸው ያለበት አካላትን ተጠያቂ በማድረግ፣ ዜጎችን በሀገራቸው በእኩልነትና በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲያመቻቹ ሰመጉ በዚህ መግለጫው ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም፡-

- ሕገ ወጥ ግድያና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ተጎጂዎችና ቤተሰቦች ተገቢው ካሣ እንዲከፈል፣
- ለሰብዓዊ መብት ጥሰቶቹ ምክንያት የሆኑትን ችግሮችና ጥያቄዎች ከሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመመካከርና በመወያየት የማያዳግም መፍትሄ እንዲሰጥ፣
- ከህግና ከዲሞክራሲ አግባብ ውጭ በዜጎች ህይወትና አካል ላይ ጥቃትና ጉዳት የፈፀሙና ያስፈጸሙ የመንግሥት አካላትን ለሕግ በማቅረብ ተጠያቂ እንዲያደርግ፣
- መንግሥት ብሔርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገውን የፌዴራል አደረጃጀት ክፍተቶችና ችግሮች በመመርመር ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርግ፣ በተለይም ዜጎች በማናቸውም የሀገሪቱ ክልል የመስራት፣ ንብረት የማፍራትና የመንቀሳቀስ መብታቸው እንዲረጋገጥ፣ እንዲሁም ከክልላቸው ውጭ የሚኖሩ ዜጎች ተገቢ ጥበቃና ዋስትና እንዲያገኙ አስፈላጊውን ተቋማዊና ሕጋዊ ስርዓት እንዲዘረጋ፣
- የብሔር ተኮር ግጭቶችን የሚያነሳሱ ቅስቀሳዎችን በመከታተል ይህን በሚያደርጉ አካላት ላይ ፈጣን እርምጃ እንዲወስድ፤
- የቅርቡን ጊዜ ጨምሮ በሐገራችን የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነጻ፣ ገለልተኛና ሣይንሳዊ በሆነ መንገድ አጣርቶ ችግሮችን በተጨባጭና በአስተማማኝ ሁኔታ ለማሳየት እንዲሁም ኃላፊነት የተሞላበትና ገንቢ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ ከሚረዱት መንገዶች አንደኛው ሐገር በቀል፤ አንጋፋና ነጻ የሆነውን የሰብዓዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅት የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔን ሰመጉን በነጻነት፣ በስፋትና በሙሉ አቅሙ የሚሰራበትን የህግ፣ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ምህዳር ማስፋት ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ለሰመጉ ተገቢውን እውቅና፣ የመሥራት ነጻነት፣ ድጋፍና ጥበቃ እንዲያደርግለት፣
- በአጠቃላይ በተለያዩ ወቅቶች በሀገሪቱ የደረሰውን የህይወት፣ የአካልና የንብረት ጥፋት ነጻና ገለልተኛ በሆነ መንገድ ለማጣራት ጥያቄ ላቀረቡ የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ጽ/ቤት፣ የአፍሪካ የሰዎችና ሕዝቦች መብቶች ኮሚሽንና ለሌሎችም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማት በጥያቄአቸው መሠረት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ምርመራ ለማድረግ እንዲፈቀድላቸው ይጠይቃል፡፡

በመጨረሻም ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍና ስልክ በመደወል ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ሰመጉ ይጠይቃል፡፡

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 80001፣ ኢ-ሜል፡- national.parliament@ethionet.et፣
  ፋክስ ፡- (+251) 011 155-0400፣የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር ፡- 20122/1000፣ ኢ-ሜል ፡- kumashih@gmail.com
  ፋክስ ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣
  የስልክ ቁጥር ፡- (+251) 011 122-3322፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ ፡- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ
  ስልክ ቁጥር +251 115541868
  ፋክስ +25115517775
  ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም:
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ ኢ-ሜል፡ ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ ኢ-ሜ፡ hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ፡ (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

- ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 257 75 34 29
  ጅግጅጋ፣ ኢትዮጵያ
- ለሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 588 ፋክስ፡- (+251) 025 775-2325፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 775-4038 / 025 775-3241
  ጂግጂጋ፣ ኢትዮጵያ
- ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣
  ባሕርዳር፣ ኢትዮጵያ
- ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499
  ባህር ዳር፣ ኢትዮጵያ
- ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣
  ሐዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 18 ፋክስ፡- (+251) 046 220-1641፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 220-9166
  ሃዋሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣
  አሶሳ፣ ኢትዮጵያ
- ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣
  መቀሌ፣ ኢትዮጵያ

- ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣
  ጋምቤላ፣ ጋምቤላ
- ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 025
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 047 551-1544
  ጋምቤላ፣ ኢትዮጵያ
- ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ
- ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 272 ፋክስ፡- (+251) 025 666-0666፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1799
  ሐረር፣ ኢትዮጵያ
- ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
  ስልክ ቁጥር (+251) 0336660056
  ሰመራ ኢትዮጵያ
- ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 11 11 358
  ፋክስ፡ (+251) 025 11 19 805
- ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት
  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363

**ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!**

**ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤**
**የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽን (FIDH) አባል፣**
**የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣**
**የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders) መሥራችና አባል ነው፡፡**